# በግብርና ዘርፍ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዚያ 2015

<u>አዲስ አበባ</u>

# ማውጫ


| | | ገፅ |
|---|---|---|
| ክፍል አንድ | መግቢያ | |
| 1.1. | የጥናቱ ዳራ | |
| 1.2. | የዘርፉ ተቋማት ሥልጣንና ተግባራት | |
| 1.3. | የጥናቱ ዓላማ | |
| ክፍል ሁለት | በግብርና ዘርፍ የሙስና ስጋት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ | |
| ክፍል ሶስት | የጥናቱ ስነ-ዘዴ | |
| 3.1. | የጥናቱ ወሰን | |
| 3.2. | የዝግጅት ምዕራፍ | |
| 3.3. | የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች | |
| 3.4. | የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ | |
| 3.5. | የጥናቱ ተግዳሮቶች | |
| 3.6. | የጥናቱ ውስንነቶች | |
| ክፍል አራት | ዘርፍ-ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና | |
| 4.1. | የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት | |
| 4.2. | ተጠያቂነትን ማስፈን | |
| 4.3. | የተቋማት ግልፅነት | |
| 4.4. | አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ | |
| 4.5. | የንብረት አስተዳደር | |
| 4.6. | የግዥ አስተዳደር | |
| 4.7. | የሰው ሃብት አስተዳደር | |
| 4.8. | የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ | |
| 4.9. | የፕሮጀክቶች አስተዳደር | |
| 4.10. | ኦዲትና ቁጥጥር | |
| 4.11. | የተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና | |
| ክፍል አምስት | ምክረ-ሀሳቦች | |
| | ማጣቀሻ ፅሁፎች | |

# ክፍል አንድ፦ መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና የአንድን አገር መልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ እድገት እና የሰብአዊ መብት መከበር በከፍተኛ ሁኔታ ከሚጎዱ ችግሮች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ሙስና ማለት ባለስልጣኖች/ሀላፊዎች ከህብረተሰቡ የተሰጣቸውን አደራ ለግል መበልጸጊያ የማዋል ብልሹ አሰራር ማለት ነው። ሐቀኝነትን የማጉደል ወይም ሕገወጥ ባህሪ ማለት ነው፡፡ ሙስና የህግ የበላይነትን በማጣመም እና ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆነውን ተቋማዊ መሰረት በማቀጨጭ ልማትን ያዳክማል፣ ለማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ማነቆ ይሆናል፣ በመሰረተ ልማት፣ በተቋማት እና በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስትመንቶችን በማዳከም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምህዳርን ያጎለብታል። የሞራል እሴቶች ማሽቆልቆል እና ህገ-መንግስታዊ ተቋማትን እና ስልጣንን አለማክበር የሙስና መገለጫዎች ናቸዉ፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል፤ አገሮች ፣ ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል። ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል። እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና/ወይም የግሉ ሴክተር ድርጅቶች ጥረታቸውን እና ሀብታቸውን በጣም አንገብጋቢ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት ህጎችን በማውጣት እና በመተግበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናትና ምርምር በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው። በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ግን ለሙስና ስጋት የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ አደረጃጅቶችና አሰራሮችን በመለየት ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ ባለመሰራቱ፣ ሙስና በየጊዜው እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ሥራን በተቋም ደረጃ የሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አደራጅቶ ወደ ተግባር ቢገባም፣ እስካሁን በተቋማቱ ውስጥ የሙስና መከላከል ተግባራት የተገኘዉ ዉጤት በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ደርሶ አልተገኘም፡፡

በተለያዩ ዘርፎች ስር በሚገኙ ተቋማት ሊከሰቱ ለሚችሉት የሙስና ዓይነቶች ፣ የህጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ ተቋማዊ ባህል፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራርብ፣ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር፣ የመረጃ አያያዝ ደካማነት ፣ ወዘተ እንደ ተቋማዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። እነዚህና

የመሳሰሉት ክስተቶች በተለያዩ ዘርፎች ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ይህን የሙስና ሥጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ ሲባል በግብርና ዘርፍ ስር ባሉ ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ የሆነ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ የሙስና መከላከያ ምክረ-ሀሳቦችን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## 1.2. የዘርፉ ተቋማት ሥልጣንና ተግባራት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 20 መሰረት ለግብርናው ዘርፍ (ለግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት) ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

የግብርና እና የደን ልማትን እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና የሕግ ማዕቀፎችን ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና የመቋቋም አቅምን ለማጠናከርም የዕለት ደራሽ ድጋፍ እና የምግብ ዋስትና የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፡፡

የግብርና ምርት ስርጭትና ግብይትን በተመለከተም በሰብል ምርት፣ በእንስሳትና ዓሳ እና የተፈጥሮ ሃብት ልማት ግብዓቶች ፍላጎት፣ አቅርቦት፣ ሥርጭትና ግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪም የግብርና ልማት በገበያ እንዲመራና ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብት የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በገበያ የሚቀርብ ማናቸውንም የሰብል ምርት፣ እንስሳትና ዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡

ከግብርና ኢንቨስትመንት እና ከግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አንፃር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የግብርና ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤ ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት አማራጮችንና እምቅ አቅሞችን ይለያል፣ የኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚስፋፉበትን ስልት ይቀይሳል፣ በዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፡፡ እንዲሁም በግብርና ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

ከፋይናንስ ሥርዓት ጋር ተያይዞ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለአርሶ አደሮች፣ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች እና በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ የግል ዘርፍ ተዋንያን ተደራሽ የሆነ የግብርናና ገጠር ፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ የግብርና የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፡፡

ከአገልግሎት አሰጣጥ እና ከቴክኖሎጂ ማስፋፋት አንፃር፣ የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት ምዝገባና ቁጥጥር ይዘርጋል፣ የምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ እንዲሁም የሰብል፣ የእንስሳትና የዓሳ ምርት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የምርት ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የግብርና ኤክስቴንሽን ምክር አገለግሎት፣ የቴክኖሎጂ እና አመራረት ስልቶች አቅርቦት እንዲስፋፋና አጠቃቀሙም እንዲያድግ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፡፡

የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምን በተመለከተ ለገጠር መሬት አስተዳደርና ለተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ዘላቂ የአጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ድጋፍም ይሰጣል፡፡ እንዲሁም በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በገበያ የሚመራ የእንስሳት ሃብት ልማት፣ ውሃን ማዕከል ያደረገ የሰብልና የእንስሳት መኖ ልማት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የግጦሽ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ልማት አጠቃቀም ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል፡፡ በተጨማሪም የተፋሰስ፣ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

**አጠቃላይ ዓላማ፡-**

የግብርና ዘርፍ ተቋማትን የአሰራር ስርዓት ከሙስና ስጋት አንፃር በመገምገም የሙስና ተጋላጭነት ትንተና ማካሄድ ነው፡፡

**ንዑስ አላማዎች፡-**

የግብርና ዘርፍ ተቋማትን፥

- የአሠራር ስርዓቶች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣
- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

## ክፍል ሁለት፡- በግብርና ዘርፍ የሙስና ስጋት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

ግብርና አፈርን የማልማት፣ ሰብል የማብቀል እና የእንስሳት እርባታ ጥበብ እና ሳይንስ ነው። የእጽዋትና የእንስሳት ተዋጽኦዎችን ማዘጋጀት እና ለገበያ ማከፋፈልን ያጠቃልላል (Rutledge et al. 2011)። በዚህ ሰፊ ፍቺ መሰረት እንደ ሁኔታው የተለያዩ ሂደቶችን እና ተዋናዮችን (ከትናንሽ ከእጅ-ወደ-አፍ እርሻ (small-scale subsistence farming) እስከ ትላልቅ የንግድ እርሻዎች) ያቀፉ ከመሆናቸው አንፃር የግብርና ዘርፎች ተፈጥሮ እና አይነት ሊለያዩ ይችላሉ (Dastrup, 2019)።

ሰፊ በሆነው ግብርና ዘርፍ ውስጥ የመሬት ባለቤትነት እና ይዞታ፣ የብድር አቅርቦት፣ የአቅርቦት ጥራት፣ የውሃ ድልድል፣ ግብይት እና የግብርና ንግድ (agribusinesses) ልማት በሙስና የመጠቃት እድል አላቸው (Fink, 2002)። ዘርፉ በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ ግንዛቤን ለማግኘት አንዱ ዘዴ የግብርና እሴት ሰንሰለቶችን መረዳት ነው። ይህ ዓይነቱ እውቀት በተለያዩ የግብርና እሴት ሰንሰለት ደረጃዎች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸውን የሙስና አደጋዎች እና የፀረ-ሙስና እርምጃዎችን ለመለየት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። አብዛኛዎቹ የግብርና እሴት ሰንሰለቶች አምስት ደረጃዎች አሏቸው። እነዚህም ግብአት፣ ምርት፣ ማቀነባበር (processing) እና ማሸግ፣ ማከማቸት (storage) እና ስርጭት እና የመጨረሻ ግብይት (end markets) ናቸው። የግብርና መሰረታዊ የእሴት ሰንሰለት መዋቅርን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከተሉት የሙስና አደጋዎች በየደረጃዎቹ ሊከሰቱ ይችላሉ።

የእሴት ሰንሰለቱ የመጀመሪያ የሆነው የግብአት ደረጃ የግብርናውን ሂደት ለመጀመር አስፈላጊ ተዋናዮችን እና ሂደቶችን ያካትታል። ይህም እንደ መስኖ፣ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የጉልበት ስራ፣ የገንዘብ ድጋፍ/አገልግሎት (ድጎማ እና የእርሻ ብድር)፣ ፍቃድ፣ ሰርተፍኬት፣ ወዘተ የመሳሰሉ ከመሬት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል (Cucagna and Goldsmith 2017; Abdulsamad et al. 2013)። እያንዳንዳቸው እነዚህ ጉዳዮች ለሙስና አደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ።

ለምሳሌ መሬት ውድ ሃብት ሲሆን በመሬት ይዞታ፣ በመሬት ባለቤትነት መብት፣ በህገ-ወጥ የመሬት ወረራ እና በመሳሰሉት ለሙስና የተጋለጠ ነው። ከዓለም አቀፍ የድርጅት ተጠያቂነት ክብ ጠረጴዛ (ICAR) እና ግሎባል ዊትነስ የተገኘ ሪፖርት እንደ ምያንማር፣ ታንዛኒያ እና ላይቤሪያ ባሉ አገሮች ውስጥ ያለ የአካባቢ ማህበረሰቦች ፈቃድ የመሬት ዝውውሮች (land transfers) እና ምደባዎች መደረጋቸውን ይጠቅሳል (Schutter, 2016)። እንዲሁም በአለም ደረጃ በፍጥነት እያደገ የመጣው የሰፋፊ መሬቶች የግብርና ልማት የአገሬው ተወላጆች መሬቶች (Indigenous lands) ውስጥ ዘልቆ መግባቱን ቀጥሏል (UN, 2021)። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ2019 ለዚህ ተግባር ተብሎ በአማዞን ላይ የተደረገው የደን ጭፍጨፋ ካለፉት 11 ዓመታት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። የደን ቃጠሎን በተመለከተም፣ “የግብርና ባለሙያዎች ሆን ብለው መሬታቸውን ለግብርና ንግድ ሥራ ለመክፈት ያደረጉት ሙከራ” እንደሆነ የአገሬው ተወላጆች እና ሌሎችም ጠቁመዋል (UN, 2021; Teixeira, 2019)። በተጨማሪም በገጠር የሚገኙ አነስተኛ አምራቾች ከመሬት ይዞታ/ባለቤትነት ጋር የተያያዘ ሙስና ሊያጋጥማቸው ስለሚችል የምግብ ዋስትናቸውንና ምርታማነታቸውን እንዳያሻሽሉ ተደርገዋል። በግብርናው ዘርፍ ያለው ሙስና በተለይ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ በሚገኙ እጅግ በጣም ድሃ በሆኑ የትናንሽ መሬት ባለቤቶች (small-scale landholders) ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ በጣም የጎላ ነው (Transparency International, 2019)።

በመንግስት ድጎማዎች እና በድጎማ ብድር (credit) ድልድል ላይ የሚስተዋሉ የሙስና ተግባራት እንዲሁም የመንግስት ኮንትራቶችን እና የእርሻ አቅርቦቶች ፈቃድን በጉቦ መስጠት ሌሎች አደጋዎች ናቸው (Zúñiga, 2018)። ለምሳሌ የአውሮፓ ፓርላማ አምስት አገሮችን (ማለትም ቡልጋሪያ፣ ቼክ ሪፑብሊክ፣ ሃንጋሪ፣ ስሎቫኪያ እና ሮማኒያ) የተመለከተ ዘገባ እንደሚያመለክተው የአውሮፓ ኅብረት ለመካከለኛ እና አነስተኛ እርሻዎች ብሎ የመደበው ገንዘብ "ከፖለቲካ ልሂቃን እና ትላልቅ ድርጅቶች (conglomerates) ጋር የተገናኙ አካባቢያዊ ኃያላን (local oligarchs) እጅ ውስጥ ወድቋል" (Đorđević, 2021)። በማደግ እና በሽግግር ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ የግብርናው ዘርፍ እንዲያብብ ከተፈለገ የብድር አቅርቦት ወሳኝ ነው። ነገር ግን በመንግስት ድጎማ የሚደገፍ ብድር ድልድል ላይ ሙስና የተለመደ ክስተት ነው። በአብዛኛው አላስፈላጊ ክፍያዎች እና የመቶኛ ክፍያዎች የመንግስት ባለስልጣናት ብድር በሚሰጡበት ጊዜ ገንዘብ አላግባብ የሚሰበስቡባቸው መንገዶች ናቸው።

እንደ ዘርና ማዳበሪያን የመሳሰሉ የግብርና ግብአቶች ላይም ተደጋጋሚ የማጭበርበር ድርጊቶች እንዳሉ ይታወቃል። በቅርቡ በህንድ ወደ 66 ሚሊዮን ዶላር አካባቢ የሚገመት ከ23,000 ኩንታል በላይ የድጎማ ማዳበሪያ በውሸት ሽያጭ (fictitious sale) ከመንግስት መጋዘን ወጥቶ ወደ ጥቁር ገበያ በእጥፍ ዋጋ መዘዋወሩን የሚገልጽ ዘገባ ወጥቷል (Misra 2020)።

በመንግስት ኮንትራቶች ወይም የግብርና አቅርቦቶች ፈቃድ ላይ ሙስና የተለመደ ነው። ደካማ ጥራት ያላቸው እቃዎች/አገልግሎቶች አቅርቦት፣ በውል መሰረት ያልቀረቡ እቃዎች (undelivered goods) እና የተጋነነ የእቃዎች ዋጋ በመንግስት ባለስልጣናት እና በግሉ ሴክተር ድርጅቶች መካከል ከሚደረግ ህገ-ወጥ ሽርክና የሚመነጩ የተለመዱ ውጤቶች ናቸው። ለምሳሌ የፊሊፒንስ የምርመራ ጋዜጠኝነት ማእከል ገበሬዎች ዝቅተኛ ጥራት ያላቸው የመትከያ ቁሳቁሶች፣ ጤናማ ያልሆኑ የእርሻ እንስሳት እና ያልተላኩ የእርሻ መሣሪያዎችን ከግዛቱ እንደተቀበሉ ዘግቧል (Sarimiento, 2000)።

ውሃ በግብአት ደረጃ ላይ ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ነው። እ.ኤ.አ. በ1980ዎቹ በህንድ ውስጥ የመስኖ አስተዳደር ስርዓቶችን የተመለከተ ዝርዝር ጥናት በዘርፉ ያለውን በርካታ የተዋረድ ደረጃዎችን ያካተተ የሙስና ስርዓት ባህሪ አጉልቶ አሳይቷል። የመስኖ መሠረተ ልማትን የሚገነቡ እና ስራው ካለቀም በኋላ የሚቆጣጠሩ ተቋራጮች በአስተዳደር ኃላፊነት ላይ ለተሰማሩ መሐንዲሶች ጉቦ መክፈል ነበረባቸው። ተቋራጮቹም በተራቸው ደረጃቸውን ያልጠበቁ አገልግሎቶች በማቅረብ አትራፊ ሆነዋል። መሬታቸው በመደበኛ መስኖ ያልተካተቱት አርሶ አደሮች ህገወጥ የውሃ አቅርቦት ለማግኘት ጉቦ እንዲከፍሉ ተደርገዋል። አጠቃላይ ስርዓቱ በአቀባዊ (vertically) የተቀናጀ ሲሆን ከሙስና የሚገኘው ገቢ ከአስተዳደር እስከ ፖለቲካ ደረጃ ድረስ በሰንሰለት የተዋቀረ ነበር። ተመሳሳይ የኪራይ ሰብሳቢነት ዘይቤዎች በባንግላዲሽ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ኔፓል፣ ፊሊፒንስ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ታይላንድ እና ዩናይትድ ስቴትስ ታይተዋል (Tacconi and Williams, 2020)።

ቀጣዩ የእሴት ሰንሰለት የምርት ደረጃ ነው። እንደ የእርሻ አሰራር እንዲሁም የሰብል ተፈጥሮና አይነት ይህ ደረጃ ነጠላ የእርሻ ክፍሎችን፣ የኅብረት ስራ ማህበራትን፣ ሰፋፊ እርሻዎችን፣ ወዘተ ሊያካትት ይችላል። ሰፋፊ እርሻዎች ውስጥ አንድ ነጠላ የሰብል ዝርያን (monoculture) የማምረት አካሄድ ብዙውን ጊዜ በሙስና የታጀበ ነው። ለምሳሌ በዓለም ላይ ትልቁን የፓልም ዘይት በማምረት ላይ

የምትገኘው ኢንዶኔዢያ የዘንባባ እርሻን ለማልማት ሰፊ የተፈጥሮ ደኖችን መንጥራለች። አብዛኛው ይህ ሂደት የሚቀጣጠለው ያለ የአካባቢ ማህበረሰቦች ተሳትፎ በግል ኩባንያዎች እና በመንግስት ኤጀንሲዎች መካከል በሚደረጉ ግልጽ ባልሆኑ ስምምነቶች ነው (Van Hagen, 2021)።

በአነስተኛና በመካከለኛ ደረጃ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራትም ከሙስና አደጋ የፀዱ አይደሉም። ይህም በማደግ ላይ ወይም በኢኮኖሚ ሽግግር ላይ ባሉ ሀገራት ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም። ለምሳሌ በአሜሪካ ውስጥ በሚኒሶታ የሚገኘው የአሸቢ የገበሬዎች ኅብረት ስራ ማህበር ዋና ስራ አስኪያጅ ከኅብረት ስራ ማህበሩ ስርቆት አከናውነዋል። በተጨማሪም በደቡብ ካሮላይና ውስጥ የትራ-ካውንቲ ኤሌክትሪክ ኅብረት ስራ ማህበር የቦርድ አባላት እራሳቸውን በጥቅማጥቅሞች እና በተጨማሪ ሽልማቶች ወይም ማበረታቻዎች (perks) አበልጽገዋል (Giannakas and Fulton, 2020)።

የግብርና ሥራውን (agribusiness) የማቀነባበር፣ የማሸግ እና የማከፋፈያ ደረጃ ውስጥ እንደ የትራንስፖርት ፈቃድ አሰጣጥ፣ ማከማቻ፣ ጥሬ/ያልተጠናቀቀ የግብርና ምርት ትክክለኛ ሂደት የመሳሰሉት ለበርካታ የሙስና አደጋዎች የተጋለጡ ናቸው (ፊንክ 2002፣ 4)። “ደላሎች” (“Middlemen”) ከገበሬዎች የእርሻ ምርቶችን እጅግ በወረደ ዋጋ ገዝተው ለሸማቾች ወይም ለሁለተኛ ደረጃ አቀናባሪዎች (processers) “አስከፊ በሆነ ዋጋ” ሲሸጡ ይስተዋላል። ትንንሽ አምራቾችም ያመረቱትን ምርት (በተለይ በቀላሉ የሚበላሹ (perishable) ምርቶችን) ለማከማቸት እና ለመያዝ ምንም አይነት አቅም/ሃብት የላቸውም (Oguoma et al., 2010)። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የገበሬዎችን ከደላሎች እና ከገዢዎች ጋር የመደራደር አቅም ይገድባል። በአለምአቀፍ ደረጃ በእርሻ ምርት ሰንሰለት ውስጥ እኩል ያልሆነ የሃይል ስርጭት ስጋት እንዳለ እና ገበሬዎች በተለይ በእነዚህ የኃይል ግንኙነቶች ውስጥ የተጎዱ መሆናቸውን ጥናቶች ይጠቁማሉ (Malak-Rawlikowska et al., 2019)።

አምራቾች ተፈላጊውን የምስክር ወረቀት ለማግኘት ተቆጣጣሪዎችን በገንዘብ ለመደለል ስለሚሞክሩ የምርት ደረጃዎች እና የምስክር ወረቀቶች ሌላ የሙስና ምንጭ ይሆናሉ። የጥራት ማሻሻያ ማዕከላት በገጠር ማህበረሰቦች መዘርጋት ምርቱን ለምርመራ በማሰባሰብ እና ለግለሰብ አምራቾች ጉቦ የመስጠት እድልን በማስቀረት የምርቶች ተጨባጭ ደረጃ አሰጣጥን ለመደገፍ ይረዳል።

ቀጣዩ የማከማቻ (storage) እና ስርጭት ደረጃ ነው። ከላይ በተጠቀሰው ደረጃ ከተጠቀሱት አደጋዎች በተጨማሪ ስርቆትና ምዝበራ የግብርና ምርቶችን በማከማቸት እና በማሰራጨት (በማከፋፈል) ረገድ የተለመዱ ችግሮች ናቸው። ለአብነት ያህል በቻይና የሊያኦኒንግ እና ጂሊን ግዛቶች መንግሥታዊ የእህል ማከማቻ ተቋማት አስተዳዳሪዎች አዲስ ለተመረተ እህል የተተመነውን ዋጋ ለከረመ እህል በመክፈል የህዝብን ሃብት ያላግባብ መዝብረዋል። በተጨማሪም በተዘረጉት የግላዊ ግንኙነቶች እና አውታረ መረቦች ስርዓት የተነሳ ለመንግስት አከፋፋዮች ለመሸጥ ግንኙነት የሌላቸው የአካባቢው ገበሬዎች ብዙውን ጊዜ ለግል ነጋዴዎች በቅናሽ ዋጋ ለመሸጥ ተገደዋል (Danning 2015)።

የእሴት ሰንሰለቶች የመጨረሻ ደረጃ የመጨረሻ ግብይት (end markets) ነው። በተለይ ትላልቅ አለምአቀፍ የንግድ ተቋማትን ሲያካትት፣ ይህ ደረጃ ብዙውን ጊዜ ውስብስብ እና ግልጽ ያልሆነ ነው (Transparency International 2019)። የ2013 የፈረስ ስጋ ቅሌት ጉዳይ ይህንን ነጥብ ያሳያል።

ሮማኒያን ለቆ የሚወጣው ስጋ ፈረስ ተብሎ ተለጥፎበት ሳለ፣ በተለያዩ ሀገሮች አልፎ ወደ ፈረንሳይ የመጨረሻ መድረሻው ሲደርስ የበሬ ሥጋ የሚል መለያ ተሰጥቶታል (Transparency International, 2019፣ Puiuleţ et al. 2013፣ Lawrence, 2013)። በዚህ ቅሌት ውስጥ የተሳተፉት ኩባንያዎችም ግልፅነት የጎደላቸው እና የትክክለኛ ባለቤቶች ማንነት እንዳይታወቅ ተደርገው የተደራጁ ነበሩ (Global Witness, 2013)። በተጨማሪም የግብፅ ጥጥ ምርቶች ላይ የተደረገው ጥናት ከፍተኛ መጠን ያለው የጥጥ ምርት ምንጩ ከግብፅ እንዳልሆነና ዝቅተኛ ጥራት ካለው ጥጥ የተሰራ መሆኑን አረጋግጧል (Subramanian, 2021)።

አንዳንድ ጊዜ በምግብ እና በግብርና ምርቶች ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች በሙስና በተዘፈቁ አውታረ መረቦች ምክንያት ከህግ ወሰን ውጭ ሊሰሩ ይችላሉ (Transparency International, 2019)። በግብርና ምርቶች ላይ የተሰማሩ የሽቀጦች ነጋዴዎች በዚህ ረገድ ጎልተው ይታያሉ። ይህ ስራ ከ75% እስከ 90% የሚሆነውን የአለም የእህል ንግድ በሚቆጣጠሩ አራት ዋናዋና ድርጅቶች በሞኖፖል የተያዘ ነው (Lawrence, 2011; Baines et al., 2021)። የሸቀጣ ሸቀጥ ነጋዴዎች ደካማ የአስተዳደር፣ የተቋማትና የህግ የበላይነት እንዲሁም እና ውስን የመንግስት ተጠያቂነት ባለባቸው መስተዳድሮች (jurisdictions) እንደሚንቀሳቀሱ ይታወቃል (Chêne, 2016)። እንዲሁም በሁሉም ዓይነት ቅሌቶች ውስጥ እራሳቸውን በማሳተፍ የሀገራቸውን ሃብት በሚያባክኑ ልሂቃን (elites) መካከል ሙስናን በማስፋፋት ይታወቃሉ (Baines et al., 2021)።

ከላይ የቀረበው ትንተና የግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ እንደ የግብርና ምርት፣ የአስተራረስ ዘዴ፣ የአሰራር አካባቢ (operational environment) እና የሚመለከታቸው ተዋናዮችን ጨምሮ በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት ሊፈጠሩ የሚችሉ የሙስና አደጋዎችን አመላክቷል። ስለሆነም የሚወሰዱት የፀረ-ሙስና ዕርምጃዎች እያንዳንዱን አውድ ትኩረት ባደረገ መልኩ ተያይዘው የሚመጡ የሙስና አደጋዎችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል። የዩናይትድ ስቴትስ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (USAID) በግብርና ላይ ያለውን ሙስና አስመልክቶ ያወጣው ሪፖርት ሙስናን ለመከላከል የሚደረጉ ጥረቶች ግልጽነት፣ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ተጠያቂነት፣ መከላከል እና ማስፈጸም (TAAPE) ላይ ማተኮር እንደሚገባቸው ገልጿል (Fink, 2002)።

## ክፍል ሶስት፦ የጥናቱ ስነ-ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ወሰን (Scope of the study)

ይህ ጥናት የተካሄደው በፌደራል የግብርና ሚኒስቴር እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተጠሪ በሆኑ ዘጠኝ ተቋማት ላይ ነው። የተጠሪ ተቋማት ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፦

- የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣
- የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት፣
- የኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን፣

- የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን፣
- የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን፣
- የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣
- የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት፣
- የኢትዮጵያ ደን ልማት፣
- የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት፣

### 3.2. የዝግጅት ምዕራፍ

በመጀመሪያ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 10 የትኩረት ርእሰ-ጉዳዮችን በመለየት የመረጃ መሰብሰቢያ ቼክ-ሊስት ተዘጋጅቷል፡፡ እነዚህ 10 ርእሰ-ጉዳዮች ማንኛውም የመንግስት ተቋም ሊተገብራቸው የሚገቡና ተመሳሳይ ባሕሪ ያላቸው አሰራሮች ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው ተቋማት ከተቋቋሙበት ዐላማ አንፃር የራሳቸው የሆነ ልዩ ባሕሪ አላቸው፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ ከተቋማቱ ልዩ ባሕሪ ሊመነጩ የሚችሉና የመለያየት ሁኔታ የሚስተዋልባቸውን የሙስና ስጋቶች ለመለየት አንድ ተጨማሪ ርእሰ-ጉዳይ ተካቷል፡፡

በመቀጠልም በተዘጋጀው ቼክ-ሊስት ዙርያ ለጥናት ቡድን አባላት (መረጃ ሰብሳቢዎች) ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎች ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ መረጃዎችን እንዴት መሰብሰብ እንደሚቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ ፈጥረዋል፡፡

### 3.3. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ቼክ-ሊስት (የዳሰሳ መጠይቅ) እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ናቸው፡፡ ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ለሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

**ቼክ-ሊስት፡-** የጥናት ቡድን አባላት የተቋማት የተለያዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በማወያየት እንዲሁም (እንዳስፈላጊነቱ) በምልከታ የተዘጋጀውን ቼክ-ሊስት እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ይህን ጥናት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በቼክ-ሊስት ላይ የተነሱ ነጥቦች አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጣቸው በሰነድ ወይም በምልከታ ሲረጋገጡ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የሙስና ግንዛቤ (perception) ጥናት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃ የተቋማት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ የተሞረኮዘ የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ነው፡፡

**ሰነዶች፡-** የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከል ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ተዳሰዋል፡
፡

**የሃሳብ ማጎልበቻ ዉይይት**፡- ከ10ሩ ርዕሰ-ጉዳዮች ጋር ታያያዥነት ያላቸውን ወይም በቀጥታ በቼክ-ሊስት ውስጥ ያላተካተቱትን የሙስና ስጋቶች በጥቂቱ ለመዳሰስ የበርካታ አመታት ዕውቀት ካላቸው በጥንቃቄ ከተመረጡ ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች (experts) ጋር ሃሳብ የማጎልበት ውይይት ተካሂዷል፡፡

## 3.4. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ነው፡፡ ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) አሀዛዊ መረጃዎችን (የፕሮጀክቶች የወጪ መረጃና አፈፃፀም፣ የግዥ አፈፃፀም ማሳያዎች፣ የውጭ እና የውስጥ የኦዲት ሪፖርት ግኝቶች፣ ወዘተ) ለመተንተን ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች (ቼክ-ሊስት፣ ሰነዶች እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ተጠቅሟል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ ቡድን መሪዎች አስተባባሪነት የጥናት ቡድን አባላት ከየተቋማቱ የተሰበሰቡትን ጥሬ መረጃዎች በዘርፍ ደረጃ በማጠቃለል ትንተና አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ አማካሪዎች በበኩላቸው የሙስና ስጋቶችን በመለየትና በመተንተን ዘርፍ-ተኮር የሙስና መከላከል ምክረ-ሀሳቦችን አስቀምጠዋል፡፡

## 3.5. የጥናቱ ተግዳሮቶች (Challenges of the study)

ጥናቱ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡-

- ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በተሟላ መልኩ ለማግኘት አስቸጋሪ ሁኔታዎች መከሰታቸው፣
- ከጥናቱ ስፋት አንፃር  የጊዜ እጥረት ያጋጠመ መሆኑ፣
- ተቋማት መረጃዎችን ለመስጠት የተሟላ የፍቃደኝነት ችግር መኖር፣
- መረጃዎች በሚሰበሰቡበት ወቅት መረጃ የሚሰጡ አካላት ያለመገኘት፣
- በዘርፉ ስር የሚገኙ አንዳንድ ተቋማት በመዋሀዳቸው ምክንያት መረጃ ለማሰባሰብ መቸገር፣
- ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በተቋማት ያለመኖር፣

## 3.6. የጥናቱ ውስንነቶች (Limitations of the study)

ይህ የዳሰሳ ጥናት ቀድሞ በተመረጡና ለሁሉም ተቋማት ተመሳሳይ በሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ በማተኮር የተሰራ ከመሆኑ አንፃር የዘርፉን የሙስና ስጋቶች ሙሉ ለሙሉ ለይቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ በሌላ አገላለፅ በዚህ ጥናት ያልተለዩ ሌሎች የሙስና ስጋቶች በዘርፉ ውስጥ እንዳሉ ይታመናል፡፡ ሆኖም ግን በቀጣይ ለሚሰሩ ጥልቅ ጥናቶች እንደ መንደርደሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል መናገር ይቻላል፡፡

# ክፍል አራት፦ ዘርፍ-ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና

የግብርና ዘርፍ የስራ አፈጻጸም እና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ትንተና በ11 ርዕሰ-ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 4.1. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የቅንነት፣ ታማኝነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ዋና እሴቶች ላይ የተመሰረተ ሥነምግባራዊ ድርጅታዊ ባህልን ለማጎልበት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ክፍሎቹ ከተሰጣቸው ኃላፊነቶች መካከል፣ የክልል እና የፌደራል ህጎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የተቋሙን የሥነምግባር ፖሊሲዎች መገምገም እና ማዘመን፣ በተቋሙ ውስጥ ካሉ የስነምግባር ጉዳዮች ጋር በተያያዙ የህግ መስፈርቶች ላይ ከፍተኛ አመራሮችን ማማከር፣ ለአመራር እና ሰራተኞች በሥነምግባር ደረጃዎች (ethical standards) ላይ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት እና መተግበር እንዲሁም የሰራተኞች የሥነምግባር ጉድለትን በተመለከተ የሚነሱ ቅሬታዎችን መገምገም እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን መምከር ይገኙበታል፡፡ የሥነምግባር ክፍሎች እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት በሰው ኃይል፣ በበጀት፣ በቁሳቁስ፣ ወዘተ መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ የዘርፉ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀት እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

በግብርና ዘርፍ ስር የሚገኙ አምስት ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸውን በአዋጅ ቁጥር 1236/2013፣ የተቀሩት አምስቱ ደግሞ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በወሰነው አደረጃጀት መሰረት አዋቅረዋል፡፡ በዘርፉ ስር የሚገኙ ግሚሱ ተቋማት በተፈቀደው የመከታተያ ክፍል የስራ መደብ የሰው ኃይል ሙሉ በሙሉ ያሟሉ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን፣ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ደን ልማት፣ የኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን እና የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት በከፊል (ከ33% እስከ 67%) ያሟሉ መሆኑን ከደብዳቤዎች እና ከተደረገ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ የሁሉም ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አመታዊ ዕቅድ እንዳላቸው እንዲሁም ምቹ የስራ ቦታ ከመፍጠር አንፃር ለሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ማሟላታቸው በሰነድ እና በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በጀትን በሚመለከት በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ አራት ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን የራሳቸው በጀት ተመድቦላቸዋል፡፡ በተቀሩት ስድስት ተቋማት ግን የበጀት ምደባን በሚመለከት መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ አስር ተቋማት ውስጥ ስምንቱ ከሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተጨማሪ የሃብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የግዢ አፅዳቂ ኮሚቴ፣ የስርዓተ ፆታ ክፍል፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ ሆኖም ግን በግብርና ሚኒስቴር እና የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ከላይ የተገለጹት አደረጃጀቶች ስለመኖራቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ በዘርፉ ስምንት ተቋማት ውስጥ የህግ ክፍል የተደራጀ መሆኑ በሰነዶች ተረጋግጧል፡፡ በኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት የህግ አገልግሎት ባለሙያ በውክልና የሚሠራ ሲሆን፣ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የህግ ክፍል እንዳለው የሚያሳይ መረጃ ግን አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ አስሩም ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሚስጥራዊነቱን በጠበቀ መልኩ ጥቆማ የሚሰጥበት፣ የሃሳብ መስጫ ሳጥን፣ ኢ-ሜይል፣ ድረ-ገጽ፣ ስልክ እና የመሳሰሉት ዘመናዊና ተደራሽ የጥቆማ መስጫ መንገዶች የተገበሩ መሆናቸውን በጥናቱ ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የተከሰቱ የሙስና ድርጊቶች እና ብልሹ ተግባራትን ለመለየት፣ ለማጣራት እና ተገቢውን የህግና አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ የጥቆማ ስርዓት አይነተኛ የትግል መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ሥር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት ይህን ስርዓት መዘርጋታቸው የሚበረታታ ነው፡፡

በዘርፍ ውስጥ የሚገኙ አስሩም ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር በቅንጅት ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ የሕግ ክፍል ራሱን ችሎ ከተቋቋመባቸው ስምንት ተቋማት ውስጥ ስድስቱ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ስርዓት ያለ ሲሆን፤ በቀሪዎቹ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ይህ አሰራር ስለመኖሩ መረጃ አልቀረበም፡፡ በአንድ ባለሙያ በውክልና በሚያሰራው የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት ውስጥም ይህ አሰራር ስለመኖሩ መረጃ አልቀረበም፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋሞቻቸው የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎችን በባለቤትነት የሚያስተባብሩ የሥራ ክፍሎች ሆነው እንደሚደራጁ ይገልፃል፡፡ በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የራሳቸው በጀት እንደተመደበላቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ስራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን በጀት የሚያገኙት በአመራሩ መልካም ፈቃድ ከሆነ ለአላስፈላጊ የአመራር ጣልቃ-ገብነት ተጋላጭ እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ በተጨማሪም በግሚሱ የዘርፉ ተቋማት የሚገኙ የሥነምግባር ክፍሎች በተሟላ የሰው ኃይል በአግባቡ አልተደራጁም፡፡ ከነዚህ ነጥቦች በመነሳት የዘርፉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለመወጣት ብቁ ቁመና ላይ አለመሆናቸውን መናገር ይቻላል፡፡
- በተወሰኑ የዘርፉ ተቋማት ብልሹ አሰራሮች ሲከሰቱ አጣርቶ ተጠርጣሪዎችን ለህግ የሚያቀርብ እና ተዛማች ስራዎችን የሚሰራ ራሱን የቻለ የህግ ክፍል እና የሃብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚፈጠሩ አደረጃጀቶች አለመኖራቸው የሙስና ስጋቶች ተብለው ሊወሰዱ ይችላል፡፡
- በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች ጋር በቅንጅት ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ ግኝት ቅንጅታዊ አሰራር መደበኛ እና የተዋቀረ (structured) የሙስናና ብልሹ አሰራር መረጃ ልውውጥ ለማድረግ፣ የጋራ ትንተና ለማካሄድ እንዲሁም የሙስና መከላከል ስትራተጂ ለመንደፍ ካለው ፋይዳ አንፃር የዘርፉ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን አለማድረጋቸውን አመላካች ነው፡፡

- በተወሰኑ የዘርፉ ተቋማት ውሎች ከመፈረማቸው በፊት በህግ ክፍል አስተያየት የሚሰጥበት አሰራር ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉ የመንግስትን ጥቅም ሊጎዱ የሚችሉ ውሎች በሙስና ድርድር/ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው፡፡

## 4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

የተጠያቂነት ስርአት የተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ለድርጊታቸው፣ ለባህሪያቸው፣ ለአፈፃፀማቸው እና ለሚወስዷቸው ውሳኔዎች ኃላፊነት የሚወስዱበት የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው፡፡ የዚህ ስርአት በአግባቡ ተግባር ላይ መዋል ማንኛውም አመራር/ሰራተኛ ከተሰጠው ስልጣንና ከተጣለበት ኃላፊነት አንፃር በአፈፃፀሙ፣ በውሳኔውና በሚያስከትላቸው ተፅዕኖዎች እንደሚገመገም እንዲሁም ብልሹ አሰራሮች መኖራቸው ከተረጋገጠ አንደአስፈላጊነቱ የእርምት እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ተጠያቂነትን ከማስፈን ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

በግብርና ዘርፍ ሥር ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ ገሚሱ በተሽከርካሪ ጥገናና ትራንስፖርት ስምሪት፣ በግዥና ንብረት አስተዳደር፣ በሰው ሃብት አስተዳደርና በመሳሰሉት የስራ ክፍሎች ላይ የሙስና ስጋት ጥናት ያካሄዱ ቢሆንም በጥናቱ መሰረት ማሻሻያዎችን ስለማድረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ ቀሪዎቹ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን፣ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ደን ልማት፣ ግብርና ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራርን በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ስለማካሄዳቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የደንበኞች እርካታ በየጊዜው በገለልተኛ አካል የሚጠና ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ተጠያቂነት ለማስፈን ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ ነው፡፡ ይህን ኃላፊነት ከመወጣት አንፃር በዘርፉ ስር የሚገኙ አምስት ተቋማት ደንቡን ያዘጋጁ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን፣ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ደን ልማት፣ ግብርና ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሥነምግባር ደንብ ስለማዘጋጀታቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት እና የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎች (በግንባታ አሸዋ ጥራት፣ በውሎ አበል፣ በሰው ሀይል ቅጥር እና በጉድጓድ ውሃ መስመር ዝርጋታ ጨረታ) እንዳሉ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በቀሪዎቹ ሰባት ተቋማት ግን ቅድመ-መከላከል ስራ እንደተሰራ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ ሰባቱ የመሰረቷቸውን ክሶች በሙሉ ወይም ሙሉ-በሙሉ በሚባል ደረጃ አሸንፈዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑት የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን የሚያሳይ ደጋፊ ሰነድ ሙሉ-ለሙሉ አላቀረቡም፡፡ ቀሪዎቹ የኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ግብርና

ባለስልጣን እና የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ክሶች ስለመመስረታቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ቅሬታዎችን በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እና በኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት ላይ 18 ቅሬታዎች ቀርበው ሙሉ በሙሉ እንደተፈቱ በውይይት የተገለጸ ቢሆንም ይህንን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ እንዲሁም ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት በስተቀር በዘርፉ ስር በሚገኙ ተቋማት የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን በበላይ አመራሮች ክትትልና ግምገማ እንደሚደረግበት የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- በዘርፉ ስር የሚገኙ ገሚሱ ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራር ላይ የሙስና ስጋት ጥናት አለማካሄዳቸው፣ እንዲሁም ሁሉም ተቋማት የደንበኞች እርካታን በየጊዜው በገለልተኛ አካል አለማስጠናታቸው ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ የሚችሉ አሰራሮችን በጥናት በመለየት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ከመፍጠር አኳያ እንደ ከፍተኛ ተግዳሮቶች ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡
- በዘርፉ ስር የሚገኙ ገሚሱ ተቋማት የሥነምግባር ደንብ በማዘጋጀት ወደ ተግባር መግባታቸው የሚበረታታ ሲሆን በቀሪዎቹ ተቋማት ግን ይህ አለመሆኑ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን መሰረት አድርጎ ሥራን ከመስራት አኳያ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡
- በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎች እንደተሰሩ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም የሙስና ስጋቶች አድገው ወደ ሙስና ከመሸጋገራቸው በፊት በመረጃዎች ላይ በመመስረት የሚወሰድ የእርምት እርምጃ አለመኖር ለሃብት ብክነትና ለደንበኞች እንግልት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- በሁሉም የዘርፉ ተቋማት በሚያስብል ደረጃ የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን በበላይ አመራሮች ክትትልና ግምገማ እንደሚደረግበት የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ይህም የተቋማት አመራሮች በተቋማቸው ለሚካሄድ የፀረ-ሙስና ትግል የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ አንፃር በቂ ትኩርት አለመስጠታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

## 4.3. የተቋማት ግልፅነት

የመንግስት ተቋማት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ግልፅነትን ሊላበሱ ይገባል፡፡ ግልፅነት ዜጎች ለህብረተሰቡ አገልገሎት ለመስጠት የተዋቀሩ ተቋማትን የስራ አፈፃፀም እንዲሁም የሚከሰቱ ችግሮችን መንስኤ እና መዘዞችን በተመለከተ በቂ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው፡፡ የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያጠቃለለ ነው፡፡ ግልፅነት የጎደለው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ምንም እንኳን መልካም ውጤት ቢመዘገብም የተአማኒነት እና ቅቡልነት ጥያቄ ሊነሳበት ስለሚችል የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል አይደለም፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለውን የግልፅነት ስራዎች በዚህ ክፍል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ዕቅድን በተመለከተ በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት አራቱ ዓመታዊ ዕቅዳቸው ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር የተገባ መሆኑን ከተሰበሰበ መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም የዕቅድና በጀት ትግበራው የተሳካ እንዲሆን አጋዥ ሚናውን ይጫወታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን፣ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን እና የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት በዕቅድ ዙሪያ ወይይት ስለማድረጋቸው የሚያመላክት መረጃ አልቀረበም፡፡ ዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ ደግሞ በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ሰባቱ በዕቅድ አፈፃፀም ላይ ግምገማ የሚያከናውኑ ሲሆን ቀሪዎቹ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት እና የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ እንደሚካሄድ በውይይት ወቅት ቢገልጹም አመላካች መረጃ አልቀረበም፡፡ በዘርፉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሲያካሂዱ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመለየት በሚያስችል መልኩ ስለመሆኑ መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ የሚገኙ ሰባት ተቋማት ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ እንደሚደረግ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በቀሪዎቹ ተቋማት ግን ይህን ሊያሳይ የሚችል መረጃ አልቀረበም፡፡ በተመሳሳይም ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ደን ልማት በስተቀር በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ቀሪዎቹ ስምንት ተቋማት በስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚመለከታቸው አካላት እንደሚሳተፉ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ እንዲሁም በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የተለያዩ ውሳኔዎች እና ቃለጉባዔዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ስድስት ተቋማት የግዥና ጨረታ ማስታወቂያ በይፋ በጋዜጣ እንደሚያሰራጩ በጥናቱ ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎች የሚያመላክቱ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ግን ይህን ስለማድረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ አብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዜጠኞች እና ሌሎች አካላት መረጃዎችን እንደሚሰጡ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት ስምንቱ መረጃ የሚሰራጭበት ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ድህረ-ገጽ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ቀሪዎቹ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት እና የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት የማህበራዊ ሚዲያ ቢኖራቸውም የማይሰራ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድ ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር የተገባ መሆኑን እንዲሁም የዕቅድ አፈጻጸም ላይ ግምገማ እንደሚካሄድ የሚያመላክት መረጃ አልቀረበም፡፡ በተመሳሳይም በስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚመለከታቸው አካላት እንደሚሳተፉ እንዲሁም የተለያዩ ውሳኔዎች እና ቃለጉባዔዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው የሚያሳይ መረጃ በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት አልቀረበም፡፡ ይህም ግልፅነትን ከማስፈን አኳያ በዘርፉ ውስጥ እጅግ አሳሳቢ የሆኑ ክፍተቶች እንዳሉ ያሳያል፡፡

- ወደግማሽ የሚጠጉት የዘርፉ ተቋማት የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን በይፋ እንደሚያሰራጩ የሚያመላክት መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ የግልፅነት ክፍተት በእርግጥ ተከስቶ ከሆነ ለሁሉም የምርት/አገልግሎት አቅራቢዎች እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ ከመንፈጉ በተጨማሪ ለጥቅም ግጭት ስለሚዳርግ ከፍተኛ የሙስና ስጋት ነው፡፡
- ለመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ መሆን ላይ ያሉ ውስንነቶች መረጃዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዳይሆኑ እንዲሁም አጠቃላይ የሚሰጡ አገልግሎቶች ለህዝብ ግልጽ እንዳይሆኑ በማድረግ ያለክፍያ ለሚሰጡ መደበኛ የተቋማት አገልግሎቶች ተገልጋዮችን ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ለመጠየቅ (ተገልጋዮች መብታቸውን በገንዘብ እንዲገዙ) በር የሚከፍት የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

## 4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ሙስናን ለመዋጋት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግ በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታቸውን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት በሚኒስቴር መ/ቤት፣ በኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት፣ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት እና በኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን በጥናቶች እና በዕለት-ተለት ስራዎች ከሚመነጩ መረጃዎች በመንተራስ አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ እየተሰራ ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ የቀረበ ሲሆን፣ ከነዚህ ስራዎች መካከልም የዕፀዋት ዝርያ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የተቋማት ውህደትን በሚመለከት የተዘጋጀ ደንብ፣ የኅብረት ስራ አደረጃጀት መመሪያ እና የተመራማሪዎች ዕድገት መሰላል መመሪያ ይገኙበታል፡፡ በቀሪዎቹ ተቋማት ግን ህጎች ስለመውጣታቸውና ስለመሻሻላቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ስልጠና ስለመስጠታቸው የሚያሳይ መረጃ በሁሉም ተቋማት አልቀረበም፡፡ በዘርፉ ስር በሚገኙ ስምንት ተቋማት ፀድቀው የሚወጡ ህጎችና መመሪያዎች በድህረ-ገጽ ተደራሽ ስለመደረጋቸው በምልከታ ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ቀሪዎቹ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት እና የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ድህረ-ገፅ ያላቸው ቢሆንም በጥናቱ ወቅት የማይሰራ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የዜጎች ቻርተርን በተመለከተ አራት ተቋም ላይ እንደተዘጋጀ በምልከታ የታየ ቢሆንም የተዘጋጀው የዜጎች ቻርተር ለተገልጋይ ተደራሽ ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በቀሪዎቹ ስድስት ተቋማት (ግብርና ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን፣ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ደን ልማት) የዜጎች ቻርተር ስለመዘጋጀቱ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ውስጥ ለአመራርና ሰራተኞች በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አተገባበር ላይ ስልጠና ስለመሰጠቱ መረጃ አልቀረበም፡፡ ይህ ጉድለት በሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ላይ ከሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ በተጨማሪ ሠራተኞች ከዕውቀት ክፍተት ጋር ተያይዞ ለብልሹ አሠራር እንዲጋለጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የዜጎች ቻርተር አለመዘጋጀቱ እና የተዘጋጀውም ቢሆን በተገቢው መንገድ ለተገልጋዮች ተደራሽ አለመደረጉ የተቋማቱ አሠራር ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዳይኖረው ሊያደርግ ስለሚችል የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
- በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት ገሚሶቹ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ ስለማከናወናቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ በየጊዜው እየተራቀቁ የመጡት የሙስና ስልቶች ነባር ህጎች ያለባቸውን ክፍተት በመጠቀም የሚሰሩ ከመሆናቸው አንፃር ህጎቹን የመፈተሽና የማሻሻል ተግባር እንደመደበኛ የተቋማት የስራ አካል ተወስዶ መሰራት ይኖርበታል፡፡

## 4.5. የንብረት አስተዳደር

የንብረት አስተዳደር ስርአት ውጤታማነት የሚለካው ከንብረት ርክክብ እስከ ማስወገድ ድረስ በየደረጃው የሚከናወኑ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ንብረቱ በአግባቡ ተጠብቆ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ሲቻል ነው፡፡ ንብረትን ከማስተዳደር አኳያ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የተገዙ ንብረቶችን መረከብ፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅ፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ያለአገልግሎት የተቀመጡትን (ወይም የአገልግሎት ጊዜያቸውን ያጨረሱትን) የንብረት አስተዳደር መመሪያን በተከተለ መልኩ ማስወገድ ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው የንብረት ቆጠራ በማካሄድ የማረጋገጥ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ካለው የንብረት አስተዳደር ስርአት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በሁሉም ተቋማት የቢን ካርድ እና የቋሚ ንብረት ምዝገባ አጠቃቀም ስርዓት ያለ ሲሆን የተሟላ የአውቶሜሽን ስራ (IFMIS-Intergrated Financial Management Information System) የተተገበረበት ሁኔታም እንዳለ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከንብረት አያያዝ ጋር በተያያዘ የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓት በግብርና ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እና የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ተግባራዊ መሆኑን በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት በስተቀር በቀሩት ዘጠኝ የዘርፉ ተቋማት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እንደተከናወነ በሰነድ ተረጋግጧል፡፡

በ2014 ዓም በሁሉም ተቋማት በስጦታ/እርዳታ እንዲሁም በሽያጭ መልክ ንብረቶች መወገዳቸው ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በግብርና ዘርፍ ስር ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ በስጦታ ወይም በእርዳታ የተወገዱት ንብረቶች የዋጋ ግምታቸው ያልታወቀ ሲሆን፣ በሽያጭ ከተወገዱ

የተሽከርካሪ ብረታ ብረት፣ ኮምፒዩተሮች፣ ጎማዎች እና ሌሎች ከዘጠኝ ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡን በጥናቱ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝራቸው ቀርቦ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግመው የሚወገዱ መሆናቸውን የሚያሳይ መረጃ የተገኘው በዘርፉ ሁለት ተቋማት (በግብርና ሚኒስቴር እና በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት) ውስጥ ብቻ ነው፡፡ በሁሉም የዘርፉ ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶች ተገቢው ጥበቃ እና አያያዝ እየተደረገላቸው መሆኑ በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓትን የተገበሩት ሶስት የዘርፉ ተቋማት ብቻ መሆናቸውን በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ስርአት አለመተግበሩ እቃዎች በበቂ መጠን በመጋዘን ባሉበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን የህዝብን ሃብት ለብልሽት እና ብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝራቸው ቀርቦ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግመው የሚወገዱ መሆናቸውን የሚያሳይ መረጃ የተገኘው በዘርፉ ሁለት ተቋማት ውስጥ ብቻ ነው፡፡ የግምገማ አለመኖር ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ንብረቶች በሙስና ድርድር እንደአላስፈላጊ ወይም ጊዜ ያለፈባቸው ተፈርጀው ሊወገዱ የሚችሉበት ሁኔታ ሊከሰት ስለሚችል የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

## 4.6. የግዥ አስተዳደር

ተቋማት ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብአቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ሚሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህን ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የዕቃና የአገልግሎት ግብአቶችና መሳሪያዎች ለሟሟላት የግዥ ስርአትን የተከተለ ስልታዊ አካሄድ ይጠይቃል፡፡ የግዥ ስርአቱ ያለበትን ደረጃ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናቱ እንደሚከተለው ተንትኗል፡፡

በዘርፉ ስር የሚገኙ ሁለት ተቋማት (ግብርና ሚኒስቴር እና የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት) የግዥ ዕቅድን የሚገመግሙ ሲሆን ቀሪዎቹ ግን ግምግማ እንደሚከናወን ቢገልጹም ይህን የሚያሳይ መረጃ ለማግኘት አልተቻለም፡፡ እንዲሁም ሁለት የዘርፉ ተቋማት የግዥ ዕቅድ አፈፃፀምን የሚገመግሙ መሆኑ በሰነድ የተረጋገጠ ሲሆን በቀሪዎቹ ስምንት ተቋማት ግን ይህን የሚያሳይ መረጃ ለማግኘት አልተቻለም፡፡

በዘርፉ ሥር የሚገኙ የተወሰኑ ተቋማት የግዥ አፈፃፀም ለማሳያ ያህል እንደሚከተለው ተመላክቷል፡-

- በግብርና ሚኒስቴር የፐሮፎርማ ግዥ ወይም በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተከናወኑ የተለያዩ ዓይነት ግዥዎች የዋጋ ግምታቸው ብር 131,344,225.70 ሲሆን፤ ያለዕቅድ የተገዙ ግዥዎች ደግሞ ብር 6,719,125.54 እንዲሁም ከአንድ አቅራቢ የተገዙ የዋጋ ግምታቸው ብር 529,776,483.22 ብር እና 271,000 USD መሆኑ፣

- የኢትዮጵያ ደን ልማት በፕሮፎርማ 2,314,557.46 ብር የሚያወጡ ዕቃዎችን ግዥ የፈፀመ ሲሆን፤ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ያለዕቅድ በ73,553,527.58 ብር እንዲሁም በፕሮፎርማ 32,417,862.00 ብር ግዥ መፈፀሙን መረጃዎች ያመለክታሉ፣
- የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን በቀጥታ ግዥ 1,064,137 እንዲሁም በዋጋ ማቅረቢያ 1,448,801 ብር ግዥ መፈፀሙን መረጃዎች ያመለክታሉ፣
- የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በቀጥታ ግዥ 1,686,401.51 ብር እንዲሁም በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ 3,415,002.41 ብር ግዥ መፈፀሙን መረጃዎች ያመለክታሉ፣

ከላይ ለማሳያነት ከቀረቡ መረጃዎች መገንዘብ የሚቻለው በርካታ የፕሮፎርማ ግዢዎች፣ ከአንድ አቅራቢ ተደጋጋሚ ግዥዎች እንዲሁም ያለዕቅድ የሚፈፀሙ ግዥዎች በዘርፉ ተቋማት መከናወናቸውን ነው::

በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት መካከል የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ከስራ ክፍሎች የሚቀርብ ፍላጎትን መሰረት በማድረግ እንዲሁም ስቶክ ውስጥ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ ግዥዎች የሚያከናውን መሆኑ በሰነድ ተረጋግጧል:: በአንፃሩ በአብዛኛው ተቋማት ግዥ ስቶክ ውስጥ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ ስለመከናወኑ በተደረገ ውይይት ቢገለፅም ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም:: በተመሳሳይም በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን እና በእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ከግዥ በፊት የገበያ ጥናት ኮሚቴ በማዋቀር ጥናት እንደሚከናወን ከተሰበሰቡ መረጃዎች መገንዘብ የተቻለ ሲሆን፣ በቀሪዎቹ ስምንት ተቋማት ግን ይህ ስለመከናወኑ የሚያመላክት መረጃ አልቀረበም:: አብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የመንግስት ኤሌክትሮኒክስ ግዥ (EGP) ስርአትን ተግባራዊ ለማድረግ የሄዱበት ርቀት የሚያበረታታ ሲሆን፣ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ግን ይህን ስርአት ተግባራዊ ስለማድረጉ መረጃ አልቀረበም:: ከ2014 የበጀት ዓመት ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት ቅሬታ የቀረበባቸው እንዲሁም የሙስና ጥርጣሬ ቀርቦባቸው የተሰረዙ ግዥዎች አልነበሩም::

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- አብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የግዥ ዕቅድ እንዲሁም የግዥ ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ግምገማ እንደሚያከናውኑ ቢገልጹም በማስረጃ ሊረጋገጥ አልቻለም:: ይህም ግልፅነት እና ተጠያቂነትን ከማስፈን አኳያ በዘርፉ ውስጥ እጅግ አሳሳቢ የሆኑ ክፍተቶች እንዳሉ ያሳያል::
- በዘርፉ ተቋማት በርካታ የፕሮፎርማ ግዢዎች፣ ከአንድ አቅራቢ ተደጋጋሚ ግዥዎች እንዲሁም ያለዕቅድ የሚፈፀሙ ግዥዎች መከናወናቸው መንግስትን ለአላስፈላጊ ተጨማሪ ወጪዎች የሚዳርግ (ከነፃ ውድድር ሊገኝ የሚችል የዋጋ ቅናሽን በማሳጣት) ከመሆኑም ባሻገር የግዥ ዕቅዶች ክፍተት እንዳለባቸው አመላካች በመሆናቸው የሙስና ስጋቶች ተብለው ሊወሰዱ ይችላል::

- በሁሉም በሚያስብል የዘርፉ ተቋማት ግዥ የሚከናወነው ስቶክ ውስጥ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ ስለመሆኑ በቃል ቢገለፅም ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ይህ ክፍተት በቂ ስቶክ ባለበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን የህዝብን ሃብት ለብልሽት እና ብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- በዘርፉ አብዛኛው ተቋማት ግዥ ሲከናወን በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ ለተጋነነ የምርቶች/አገልግሎቶች ዋጋ ስለሚጋብዝ የሙስና ስጋት ነው፡፡

## 4.7. የሰው ሃብት አስተዳደር

የአንድን ተቋም ስኬት ከሚወስኑ መሰረታዊ ግብአቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ያላቸው የሰው ሃብት ነው፡፡ ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ሃብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የሰው ሃብት አስተዳደር ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ስምንት ተቋማት የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የቅሬታ ኮሚቴ በማቋቋም ስራ እየሰሩ መሆኑን ከተቋማት የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ቀሪዎቹ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት እና ግብርና ሚኒስቴር እነዚህን ኮሚቴዎች በማቋቋም ስራ እየሰሩ ስለመሆኑ ቢገልፁም መረጃ አልቀረበም፡፡ በአራት የዘርፉ ተቋማት በአጠቃላይ 324 ቅሬታዎች ቀርበው አብዛኛው በውይይት የተፈቱ መሆኑን በጥናቱ ወቅት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህም በመነሳት በተቋማት ቅሬታዎችን በማስተናገድ እና መፍትሔ በመስጠት በኩል ውጤታማ ሊባል የሚችል ስራ መሰራቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡

የሰራተኛ ቅጥር ለመፈፀም አብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ማስታወቂያዎችን በጋዜጣ ወይም በመገናኛ ብዙሀን የማስተዋወቅ ስራ እየሰሩ መሆኑን፣ እንዲሁም የሰራተኞች ምደባና ዕድገት በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ስርአት መዘርጋታቸውና ሕጉን በተከተለ መልኩ እየተሰራ መሆኑን ከተሰበሰቡት መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአንፃሩ ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ሰነድ የማጣራት ስራ በማናቸውም የዘርፉ ተቋማት መረጃው እስከተሰበሰበበት ጊዜ ድረስ እየተሰራ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ የስራ ኃላፊዎች ምደባ በውድድር ላይ የተመሰረተ እና ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሰረት እየተካሄደ መሆኑን ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት እና በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ (Automated) የሰው ሃብት መረጃ ስርአት እየተተገበረ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ የቀረበ ሲሆን፣ በቀሪዎቹ ስምንት ተቋማት ግን የማደራጀት ጅምር ስራዎች እንዳሉ ቢገለፅም መረጃውን ማግኘት አልተቻለም፡፡ ስልጠናን በተመለከተ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው የግብርና ሚኒስቴር እና የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ለአመራርና ሰራተኞች በተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች

ላይ የሥነምግባርና የሙያ ማጎልበቻ ስልጠናዎችን ሰጥተዋል፡፡ ቀሪዎቹ ተቋማት ግን ስልጠናዎች መስጠታቸውን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- በዘርፉ የተወሰኑ ተቋማት የዲሲፕሊን እና የቅሬታ ኮሚቴዎች እንደተቋቋሙ የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በግልፅኝነት ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት አዳጋች በማድረግ ተቋማቱን ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡
- በዘርፉ ተቋማት ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ የማጣራት ስራ አለመሰራቱ ያለበቂ ችሎታ እና የስራ ልምድ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ሊኖሩ የሚችሉበትን ክፍተት በመፍጠር የመንግስት ሃብት ያላግባብ ጉዳት እንዲደርስበት እንዲሁም ጥራት ለጎደለው የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ሊዳርግ ይችላል፡፡
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የሰው ሃብት አስተዳደር አለመገንባቱ ውሳኔዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በዘርፉ ተቋማት በሥነምግባር ዙሪያ የስልጠናዎች አለመኖር አመራርና ሰራተኞች በሥነምግባር ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ በማዳበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዲፀየፉና እንዲታገሉ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት በሚፈለገው ልክ ከግብ እንዳይደርስ ሊያደርገው ይችላል፡፡
- በተወሰኑ የዘርፉ ተቋማት የቅጥር ማስታወቂያዎችን በጋዜጣ ወይም በመገናኛ ብዙሀን የማስተዋወቅ ስራ ስለመከናወኑ የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩ የሰራተኛ ቅጥር ግልፅነት እንዳይኖረው ብሎም ለሙስና ተጋላጭ እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡

## 4.8. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

የሃብት ምዝገባ ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ተቋማዊ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይጋጩ በራሳቸው መንገድ እንዲመሩ ለማድረግ፣ አላግባብ የተገኘ ምንጩ ያልታወቀ ሃብትን ለማጋለጥ እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ትልቅ ፋይዳ ያለው ስርዓት ነው፡፡ ሥርዓቱ በተባበሩት መንግስታት የፀረሙስና ስምምነት፣ በአፍሪካ ኅብረት የሙስና መዋጊያ እና መከላከያ ስምምነት እንዲሁም የዓለም አቀፍና የአህጉር አቀፍ የፀረ-ሙስና ስምምነቶችን ተቀብለው በሚፈፅሙ ሀገራት እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም ሥርዓቱን ባለፉት አሥር ዓመታት ስትተገብር ቆይታለች፡፡ ሃብትና የገቢ ምንጫቸውን ማስመዝገብ ካለባቸው አካላት መካከል የፌደራል ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በዚህም መሰረት በ2013 በጀት ዓመት በሁሉም የግብርና ዘርፍ ተቋማት አብዛኛው የሃብት ምዝገባ ማድረግ የሚገባቸው አመራሮችና ሰራተኞች ሀብታቸውን አስመዝግበዋል፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ከ331 ሰራተኞች 74ቱ እንዲሁም በግብርና ትራንስፎሜሽን ኢንስቲትዩት 35 አመራርና ሰራተኞች የሃብት ምዝገባን በዳርስ ወይም በሲስተም እንዳከናወኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የዘርፉ ተቋማት በዚህ ረገድ የሚበረታታ ስራ ሰርተዋል ማለት ይቻላል፡፡

## 4.9. የፕሮጀክቶች አስተዳደር

ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ እስከ ፍፃሜቸው ድረስ አግባብነት ያላቸውን ህጎችና መስፈርቶች ተከትለው እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ቴክኒካል ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ የተለየ የኦዲት መዋቅር ባለመኖሩ፣ በተለያዩ አካላት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ለጥራት መጓደልና ብክነት እየተጋለጡ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክትን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ፣ በጀትና የጥራት ደረጃ ለማጠናቀቅ የዲዛይን ጥራት፣ የጨረታ አወጣጥ ሂደት፣ የክፍያ ስርአት፣ የኮንትራት አስተዳደር እና ከመሰል ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የተጠናከረ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ያፈልጋል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የግንባታ ፕሮጀክት አስተዳደር ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ውስጥ ከሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ውስጥ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ፣ ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ የተሰጠባቸው፣ የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸው፣ ውል የተቋረጠባቸው እንዲሁም ተቋራጮች ላይ ክስ የተመሰረተባቸው ወይም ተቋራጮች ክስ የመሰረቱባቸው እንዳሉ በሰነድ ተረጋግጧል፡፡ ጥቂቶቹ ከታች ተዘርዝረዋል፦

- በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ (የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች መካከል የደቂቅ አካላትና እንስሳት ላቦራቶሪ ግንባታ ፕሮጀክት በተያዘለት የጊዜ ገደብ ባለመጠናቀቁ ብር 13,343,263.30 መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ እንዲጋለጥ ያደረገ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች ውስጥ አምስቱ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ መሆኑ፣ የግብርና ሚኒስቴር እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁት ብር 10,730,215.03 መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ እንዲጋለጥ ያደረጉ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ደን ልማት እያስገነባቸው የሚገኙ ሁለት የደን ምርምር ማዕከላት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ መሆኑ)፣
- ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ የተሰጠባቸው (የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት የደቂቅ አካላትና እንስሳት ላቦራቶሪ ግንባታ ፕሮጀክት ብር 28,226,001.24 ተጨማሪ ስራ የተሰጠበት፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች በሶስቱ ላይ ተጨማሪ ስራ በብር 2,625,255.29 የተሰጠበት ሁኔታ፣ የግብርና ሚኒስቴር እያስገነባቸው ከሚገኙ የፕሮጀክት 66,980,025.06 ብር ተጨማሪ ስራ የተሰጠበት)፣
- የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት (የግብርና ትራንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች 10 የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላት ግንባታ ተጨማሪ 104 ሚሊዮን ብር የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት መሆኑ)፣
- ውል የተቋረጠባቸው እና ተቋራጩ ክስ የተመሰረተበት/የመሰረተበት (የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች ተቋራጩ የጠፋበት/ውል የተቋረጠበት የፍቼ ዱፕሊኬቲንግ ጂን ባንክ ግንባታ እንዲሁም ተቋራጩ የተከሰሰበት የባህርዳር ዙሪያ ሜጫና ወንዳጣ ፕሮጀክት፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች ዘጠኙ

ላይ ውል የተቋረጠ መሆኑ፣ አንድ ተቋራጭ ላይ ክስ የተመሰረተበት እንዲሁም አንድ ተቋራጭ በኢንስትቲዩቱ ላይ ክስ የመሰረተበት መሆኑ)፣

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ የሚሰጥበት አሰራር (Variation work order) ምናልባት ቀድሞ የፕሮጀክቱን ዕቅድ በተገቢው መንገድ ከመገምገምና የሚሰሩ ስራዎች አስቀድመው እንዲካተቱ ከማድረግ አንፃር ክፍተት እንዳለ ጠቋሚ ነው፡፡
- የዋጋ ማስተካከያ በተለያዩ ግንባታዎች ላይ የሚሰጥበት አሰራር ከዕቃዎች የዋጋ መናር አንፃር የመነጨ ሊሆን ቢችልም፣ ከአላግባብ የጥቅም ግንኙነት ጋር ተያይዞ የመምጣት ዕድል ሊኖረው ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡
- የፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያለመጠናቀቅ (ይህም ለተጨማሪ ከፍተኛ ወጪ መዳረጉ) ከፕሮጀክቶች አስተዳደር የክትትልና ቁጥጥር መላላት ሊመነጭ የሚችል አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡
- የበርካታ ውሎች መቋረጥ በጨረታዎች ሂደት ላይ ጥርጣሬን ይፈጥራል፡፡

## 4.10. ኦዲትና ቁጥጥር

ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣትና ሕጋዊና ጤናማ የሆነ የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ የፋይናንስና ንብረት ክንውን የውስጥ ኦዲት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡ ፡ በተጨማሪም የስራቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመ የውጭ/የውስጥ ኦዲተር የማስገምገም ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚሁ ዳራ የዘርፍ መስሪያ ቤቶች የኦዲት አስተዳደር ስርአት በጥናቱ የታየ ሲሆን በግብርና ዘርፍ ዉስጥ ባሉ ድርጅቶች ያለው አሰራር እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

በዘርፉ ያሉ ዘጠኝ ተቋማት በየአመቱ የውስጥ ኦዲት ስራ እየሰሩ መሆናቸዉን ከሪፖርቶች መገንዘብ የተቻለ ሲሆን፣ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ኦዲት ስለማከናወኑ ግን መረጃ አልቀረበም፡፡የውጭ ኦዲትን በተመለከተ በሶስት የዘርፉ ተቋማት ላይ እንደተከናወነ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን በቀሪዎች ተቋማት ግን ይህ ስለመከናወኑ ሰነድ አልቀረበም፡፡

ከውስጥ እና ውጭ ኦዲት ግኝቶች የሚከተሉት ይገኙበታል፦

- በግብርና ሚኒስቴር ለተለያዩ ቅድመ-ክፍያዎች የተከፈለና ያልተወራረደ ሂሳብ ብር 92,025,585.57፣
- የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት ለግንባታ ስራ ተቋራጭ፣ ለደመወዝ፣ ወዘተ ከተከፈሉ ቅድመ-ክፍያዎች ውስጥ ያልተወራረደ ብር 45,248,502.63 (የውስጥ ኦዲት)/ ብር 42,870,851.04 (የውጭ ኦዲት)፣
- በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ከቅድመ-ክፍያ፣ ከስራ ማስጀመሪያ እና ከሌሎች ያልተወራረደ ብር 1,489,401.50፣
- የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ለፕሮጀክት ከወጣ ወጪ ያልተወራረደ ብር 36,411,274.58 (የውስጥ ኦዲት)/ ብር 40,850,865.91 (የውጭ ኦዲት)፣

- የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ከአምስት ድርጅቶች ያልተወራረደ ብር 2,103,422.97፣
- የኢትዮጵያ ደን ልማት ከግንባታ ቅድመ-ክፍያ እና ከልዩ ልዩ ክፍያዎች ያልተወራረደ ብር 136,110,314.04፣
- የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ከኮንትራት-ቅድመ ክፍያ ያልተወራረደ ብር 168,638.31 (የውስጥ ኦዲት)/ ብር 165,507.69 (የውጭ ኦዲት)፣
- በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በውጪ ኦዲት የተገኘ ያልተወራረደ ሂሳብ ብር 6,270,596.33 እንዲሁም በውስጥ ኦዲት የተገኘ ለምን ስራ እንደሆነ በግልጽ ባልታወቀ የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦ የተገኘ ብር 284,080.11፣

በተጨማሪም ያላግባብ የተወሰዱ ክፍያዎች በተወሰኑ ተቋማት መኖራቸውን ከሪፖርቶቹ መገንዘብ ተችሏል። በየተቋማቱ ያሉ አመራሮች የውስጥ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ የማካሄድ ልምድ ያላቸው መሆኑ በሰነድ ተረጋግጧል። በተጨማሪም አብዛኛው የዘርፉ ተቋማት በውስጥ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች ላይ ተመስርተው ማሻሻዎች ማድረጋቸውን ለገንዘብ ሚኒስቴር ከተላኩ ሪፖርቶች መገንዘብ ተችሏል። በተመሳሳይም የውጭ ኦዲት በተደረገባቸው ተቋማት የማስተካከያ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆኑንም ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል። በኦዲት የተለዩ ክፍተቶች ወደፊትም የሚደጋገሙበት ሁኔታ እንዳይፈጠር፣ የመንግስት ሃብት እንዳይባክን እና ውዝፍ እየበዛ እንዳይሄድ የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑ የሚበረታታ ቢሆንም በተጠናከረ መልኩ ሊቀጥል የሚገባ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም ሁሉም የዘርፉ ተቋማት የውስጥና የውጭ የኦዲት ግኝቶች ግልጽነትን ከማስፈን አንፃር ተደራሽ የሚደረጉበትን አሰራር መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል።

ሂሳብ በወቅቱ ያለማወራረድ እንዲሁም ያላአግባብ የተወሰዱ ሂሳቦችን ክትትል በማድረግ በጊዜው እንዲመለስ ያለማድረግ የዘርፉ የሙስና ስጋቶች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ። በአጠቃላይ በመጠይቁ ከተቀመጡ ጉዳዮች አንፃር ሲታይ፣ የዘርፉ ተቋማት የኦዲትና ቁጥጥር ስርአት በመልካም ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ጥናቱ አሳይቷል።

## 4.11. የተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና

በግብርና ዘርፍ ተቋማት የበርካታ አመታት ዕውቀት ካላቸው በጥንቃቄ ከተመረጡ ሃላፊዎች እና ሰራተኞች ጋር ሃሳብ የማንሸራሸር ውይይት በማካሄድ ለሙስና ስጋት የሆኑ አሰራሮችና ሂደቶች (processes) ከነደረጃቸው እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡-

### 1. ግዥ አስተዳደር

**የስጋት ደረጃ፦** ከፍተኛ

**የስጋቱ መንስኤዎች፦** የግዥ በዕቅድ አለመመራት፣ የፕሮፎርማ ግዥ መብዛት፣ የጥራት ቁጥጥር ማነስ፣ የስፔስፊኬሽን ግልፅ አለመሆን፣

### 2. ንብረት አስተዳደር

**የስጋት ደረጃ፦** ከፍተኛ

**የስጋቱ መንስኤዎች፦** የንብረት ማስወገድ ሂደት ግልፅ አለመሆን፣ በስቶክ እያለ ተጨማሪ ንብረቶች ግዥ እንዲፈፀሙ ማድረግ፣ የንብረት ቁጥጥር መላላት (መገለጫ፦ የንብረት መጥፋት)፣

### 3. ፕሮጀክት አስተዳደር

**የስጋት ደረጃ፦** ከፍተኛ

**የስጋቱ መንስኤዎች፦** የስፔስፊኬሽን ጥራት መጉደል፣ የግንባታ መጓተት፣ የግንባታ የውል አስተዳደር ግልፅ አለመሆን፣

### 4. የመድሐኒትና መኖ ኢንስፔክሽን

**የስጋት ደረጃ፦** ከፍተኛ

**የስጋቱ መንስኤዎች፦** በቴክኖሎጂ የታገዘ የመድሐኒትና መኖ ቁጥጥር ስርአት በሚፈለገው መልክ አለመኖር (መገለጫ፦ ጥራታቸውን ያልጠበቁ መድሐኒቶች አቅርቦት)

### 5. መሰረታዊ አገልግሎት

**የስጋት ደረጃ፦** መካከለኛ

**የስጋቱ መንስኤዎች፦** የተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም አሰራር ላይ በቂ ክትትልና ቁጥጥር ማነስ (መገለጫ፦ አግባብ ያልሆነ ተደጋጋሚ የነዳጅ ቅጂ መፈፀም፣ የነዳጅ ጌጅ መበላሸት)፣ የተሽከርካሪዎች ስምሪት ላይ የክትትልና ቁጥጥር ማነስ (መገለጫ፦ ከተፈቀደላቸው አካላት ውጭ ተሽከርካሪዎችን ይዞ መታየት)፣

## ክፍል አምስት፦ ምክረ-ሀሳቦች

በዚህ ውስን ዳሰሳና ትንተና ጥልቅ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ ቢያስቸግርም የሚከተሉትን ጥቅል የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፦

- ግዥ አስተዳደር ላይ የተነሱትን እንደ በዕቅድ አለመመራት (ያለዕቅድ የሚከናወኑ ግዥዎች)፣ የፐሮፎርማ ግዥ መብዛት፣ የዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ማነስ፣ የስፔስፊኬሽን ግልፅነት መጉደል እና በስቶክ እያለ ተጨማሪ ንብረቶች ግዥ መፈፀም የመሳሰሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶችን ለመቀነስ/ለማስወገድ የዘርፉ ተቋማት የግዥ ዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና ቁጥጥር ላይ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል።
- ማንኛዉም ግዥ ከመከናወኑ በፊት የገበያ ጥናት በሚገባ ማካሄድ ወይም ጥናት ከሚያከናውኑ ህጋዊ ተቋማት መረጃዎችን በመውሰድ ጥቅም ላይ ማዋል ቢቻል፣
- የሚወገዱ ንብረቶች በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግመው የሚወገዱበትን ስርአት ተቋማቱ ሊተገብሩ ይገባል።
- የሚመለከታቸው ተቋማት በቴክኖሎጂ የታገዘ የመድሐኒትና መኖ ቁጥጥር ስርአት በሚፈለገው መልክ በማደራጀት ወደ ተግባር መግባት ይኖርባቸዋል።
- ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቅ እንዲችሉ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ፣ ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ (ውል) የሚሰጥበትን አሰራር ለመቀነስ ቀድሞ

የፕሮጀክቱን ዕቅድ በተገቢው በመገምገምና የሚሰሩ ስራዎች አስቀድመው እንዲካተቱ በማድረግ ሙስናን ለመከላከል ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

- በዘርፉ ተቋማት ውስጥ የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸው ግዙፍ የሆነ በጀት የሚያንቀሳቅሱ ፕሮጀክቶች መኖራቸው በጥናቱ ለማየት ተችላል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች ለሙስና እና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ በመሆናቸው ለቀጣይ በፕሮጀክት አስተዳደር ዙሪያ ጥልቅ የሆነ ጥናት ሊደረግ ይገባል፡፡
- የዘርፉ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በቂ ቁመና ኖሯቸው ተልዕኳቸውን እንዲወጡ በተገቢው የሰው ኃይል እና በጀት ማደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የሙስና መከላከል ስትራተጂ ለመንደፍ ካለው ፋይዳ አንፃር ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር የሙስናና ብልሹ አሰራር መረጃ ልውውጥ ማድረግና የጋራ ትንተና ማካሄድ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በዘርፉ ስር የሚገኙ ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራር ላይ የሙስና ስጋት ጥናት በማካሄድ እንዲሁም የደንበኞች እርካታን በየጊዜው በገለልተኛ አካል በማስጠናት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ የሚችሉ አሰራሮችን በመለየትና የማሻሻያ እርምጃ በመውሰድ የሙስና መከላከል ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡
- የዘርፉ ተቋማት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና ነዳጅ አጠቃቀም ላይ በቂ የክትትልና ቁጥጥር ስርአት መገንባት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በተቋማቱ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃና ስራ ልምድ የማጣራት ስራ ያልተከናወነ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በሃገሪቱ ከሚታየዉ የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት አንፃር ተቋማቱ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩት የሚገባ ጉዳይ መሆን ከግምት ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## ማጣቀሻ ፅሁፎች


1. Abdulsamad, A., Brun, L., and Gereffi, G. 2013. Realizing the potential of African agriculture: innovations and market access for smallholder farmers. Duke Center on Globalization, Governance & Competitiveness.
2. Baines, J. Open Democracy, Hager, B. S. 2021. Commodity trading: The shadowy industry destroying the planet. Equal Times.
3. Cucagna, M. E., and Goldsmith, P. D. 2018. Value adding in the agri-food value chain. International Food and Agribusiness Management Association.
4. Danning, M. 2015. CCTV uncovers corruption in China's grain storage SOE. China Daily.
5. Dastrup, A., R. 2019. Introduction to human geography. Chapter 6.2. Press Books.
6. Đorđević, N. 2021. Fraud, corruption, and misuse of EU agricultural funds a major problem in CEE, say MEPs. Emerging Europe.
7. Fink, R. 2002. Corruption and the agricultural sector. Management Systems International and USAID.
8. Giannakas, L. and Fulton, M. E. 2020. Corruption and cooperative organizations. Agricultural Economics.
9. Global Witness. 2013. Opaque structure of horsemeat company shows need for company reform.
10. Lawrence, F. 2011. The global food crisis: ABCD of food – how the multinationals dominate trade.
11. Lawrence, F. 2013. Horsemeat scandal: The essential guide. The Guardian.
12. Malak-Rawlikowska, A., Milczarek-Andrzejewska, D. and Fałkowski, J. 2019. Farmers' Bargaining
13. Power and Input Prices: What Can We Learn from Self-Reported Assessments? Special Issue Agrifood Value Chains in Developed and Developing Countries: Issues and Perspectives.
14. Misra, A. 2020. Uttar Pradesh wakes up to Rs500 crore fertiliser scam. India Today.
15. Puiuleţ, R., Bojin, D. and Radu, P. 2013. Offshore Secrecy: The horsemeat scandal. Organized Crime and Corruption Reporting Project (OCCRP).
16. Rutledge, K., Costa, H., Sprout, E., Teng, S., McDaniel, M., Boudreau, D., Ramroop, T., Hunt, J. and Hall, H. 2011. The art and science of agriculture. National Geographic Encyclopaedia.
17. Sarimiento, P. 2000. Agriculture Weighed Down by Corruption and Waste. Philippine Center for Investigative Journalism. http://www.pcij.org/stories/2000/agri.html
18. Schutter, O. E. 2016. Tainted lands: Corruption in large-scale land deals. International Corporate Accountability Roundtable (ICAR) and Global Witness.
19. Subramanian, S. 2021. Food fraud and counterfeit cotton: The detectives untangling the global supply chain. The Guardian.
20. Tacconi, L and Williams, D. A. 2020. Corruption and anti-corruption in environmental and resource management. Annual Review of Environment and Resources.
21. Teixeira, M. 2019. Brazil Amazon deforestation soars to 11-year high under Bolsonaro. Reuters.
22. Transparency International. 2019. Rotten deals: How corruption spoils our food.
23. United Nations (UN) Department of Economic and Social Affairs. 2021. State of the world's Indigenous peoples rights to lands, territories and resources. 5th Volume.
24. Van Hagen, I. 2021. Palm oil operations in Indonesia harm communities, foster corruption. Organized Crime and Corruption Reporting Project (OCCRP).
25. Zúñiga, N. 2018. Land corruption: Topic guide. Transparency International.